# ምዕራፍ ሦስት

# ልቦለድ

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ የረጅም ልቦለድን ምንነትና ባህሪያት ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ከምታነቡት ረጅም ልቦለድ መካከል መቼትንና ጭብጥን እየለያችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ታቀርባላችሁ፡፡
- ✓ ተራና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን ለይታችሁ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ከምታነቡት ረጅም ልቦለድ ውስጥ አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን እንዲሁም ሐረጋትን ለይታታችሁ ትናገራላችሁ፡፡
- ✓ የአንቀጽ ቅርጾች በኃይለ ቃልና በአረፍተነገሮች አቀማመጥ መሠረት እንደሆነ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ የተሰጣችሁን መመሪያ በመከተል መልመጃዎችን ትሠራላችሁ፡፡

© MoE, FDRE, Not to be republished

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት ከመምህራችሁ በሚሰጣችሁ መመሪያ መሠረት በዚህ ሠንጠረዥ ውስጥ የ‹‹ሀ›› እና የ ‹‹ለ›› አምድን አሟሉ፡፡ ምንባቡን ካነበባችሁ በኋላ ደግሞ የ‹‹ሐ›› አምድን ሙሉ፡፡

| | ‹‹ሀ›› ስለረጅም ልቦለድ ምን አውቃለሁ? | ‹‹ለ›› ከምንባቡ ምን ማወቅ እፈልጋለሁ? | ‹‹ሐ›› ምን አዲስ ነገር ተማርሁ? አውቃለሁ ያልኩትስ ትክክል ነበር? |
|---|---|---|---|
| ምሣሌ | ሀ) የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ ነው<br>✓ … | ✓ ስለረጅም ልቦለድ ባህሪያት<br>✓ … | |
| | ✓ … | ✓ … | |
| | 1. … | | |
| | 2. … | | |

## ረጅም ልቦለድ

ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ የሚመነጭ የሰውን ህይወት ልዩ ልዩ መልኮች በተመሳስሎ ለመቅረጽ የሚችል በቁሙ ግን እውነት ያልሆነ የኪነጥበብ ሥራ ነው። ልቦለድ በቁሙ እውነት አይደለም ሲባል የተተረከው የገጸ-ባህሪያት ህይወት በእውኑ ዓለም በእርግጥ የተፈጸመ አይደለም ማለት ነው፡፡

ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድና አጭር ልቦለድ ተብሎ በሁለት ዓበይት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡፡ አጭር ልቦለድና ረጅም ልቦለድ በፈጠራ ጽሑፍነታቸው ተመሳሳይነት ሲኖራቸው በመጠን ግን ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡

ረጅም ልቦለድ ስሙ እንደሚያመለክተው ረዘም ያለና በስድ ጽሑፍ የሚቀርብ የፈጠራ ድርሰት ቅርጽ ነው። ረጅም በመሆኑ በሚቀርበው ታሪክ ውስጥ በርካታ ገጸ-ባህሪያትን ማሳተፍ ከመቻሉም በላይ የእነዚህን ገፀ ባህሪያት ህይወት ከልደት እስከ ሞት በስፋትና በጥልቀት ለማሣየት በቂ ቦታና ጊዜ አለው። በዚህ ዓይነቱ የፈጠራ ድርሰት ውስጥ በእውናዊው ዓለም ያሉ ሰዎች የሚገጥሟቸው ደስታና ሃዘን፤ ፍቅርና ጥላቻ፤ ማግኘትና ማጣት፤ ምኞትና ተስፋ፤ ባጠቃላይ የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎችና ልዩ ልዩ አመለካከቶች ለዛ ባለው መንገድ ሰፋ ባለ ሁኔታ እውን መስለው ይቀርባሉ። አንባቢም በታሪኩ የተሳተፈ እየመሰለው ህይወትን እንዲታዘብ፣ የራሱንም ማንነት እንዲያጤንና እንዲመራመር እድል ይሰጣል። አጭር ልቦለድ የራሱ ቅርጽና ይዘት ያለው የፈጠራ ድርሰት ነው። ከረጅም ልቦለድ የሚለይባቸውም ሶስት መሰረታዊ ባህሪያት አሉ። እነሱም ጥድፊያ፣ ነጠላ ውጤትና ቁጥብነት ናቸው። አጭር ልቦለድ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ ወደ ፊት ሲገሠግስ ረጅም ልብወለድ ጊዜ ስላለው አይጣደፍም። አጭር ልቦለድ አንድን ጉዳይ ብቻ መርጦ በትኩረት ሲያይ ረጅም ልብወለድ ግን ብዙ ጉዳዮችን ይዳስሳል። አጭር ልቦለድ ዝርዝር ነገሮችን ከማንሳት ተቆጥቦ በአጭሩ ሲያቀርብ ረጅም ልብወለድ ግን ዝርዝር ባለ ሁኔታ ነገሮችን ለማብራራት ስለሚጓዝ ቁጥብነት አይታይበትም።

*(ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ፣ ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ ለ 11ኛና ለ 12ኛ ክፍል፣ 1999 እና ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን፣1992)*

## ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

**ሀ. የምንባቡን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን "ሐሰት" በማለት መልሱ።**

1. በአንድ ልቦለድ ውስጥ የግለሰብ አልያም የማህበረሰብ የህይወት ገጠመኝ ፈጠራዊ በሆነ መንገድ ሊቀርብ ይችላል።

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

© MoE, FDRE Not to be republished

2. በልቦለድ ዓለም የሚሳሉ ገጸባህሪያት በገሃዱ ዓለም ላይ ሲኖሩ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
3. ረጅም ልቦለድ በባህሪው መጠነ ሰፊ በመሆኑ ደራሲው ከአንድ በላይ ጭብጥ የማሳየት እድል ይኖረዋል፡፡
4. የአንድ ልቦለድ ታሪክ በገሃዱ ዓለም ላይ ለመከሰቱ በማስረጃ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡
5. ልቦለድ ሰዎች ካነበቡት ታሪክ ማንነታቸውን እንዲፈትሹ እንዲሁም የህይወትን ገጽታዎች ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱ ንቃተ ህሊናቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛል፡፡

**፪. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ በ"ሀ" ክፍል ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ(አቻ) የሆኑትን በ"ለ" ክፍል ከቀረቡት በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ምናብ | ሀ. ገሀድ |
| 2. እውን | ለ. ዝርው |
| 3. ነጠላ | ሐ. ዋና |
| 4. አጤነ | መ. አንድ |
| 5. ዓብይ | ሠ. ሀሳብ |
| | ረ. አገናዘበ |

**፫. ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን በመምረጥ መልስ/ሽ/፡፡**

1. ከሚከተሉት ውስጥ ስለልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ልቦለድ ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት ያለው ሰው በሙሉ ሊጽፈው የሚችለው ጥበብ ነው፡፡
   - ለ. የልቦለድ ታሪክ በመረጃ የተደገፈ እንዲሆን ይጠበቃል፡፡
   - ሐ. ልቦለድ በሰው የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴንና ገጠመኝን መሠረት አድርጎ የሚጻፍ የፈጠራ ድርሰት ነው፡፡
   - መ. በልቦለድ የማስዋብ ወይም የማጋነን ሁኔታ አይፈቀድም፡፡

2. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል የረጅም ልቦለድ ባህሪይ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ጠባብ መቼት
   ለ. በርካታ ገፀባህሪያት
   ሐ. ከአንድ በላይ ጭብጥ
   መ. ሰፊ የገፀባህሪያት ገለፃ

3. አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ከሚለይባቸው ባህሪያት አንዱ “ቁጥብ” መሆኑ ነው። የዚህን ዐረፍተ ነገር ሐሳብ የሚያጠናክረው ከቀረቡት አማራጮች መካከል የትኛው ነው?
   ሀ. ነገሮችን ግራ ቀኝ እየመዘነ እና እየገመገመ ታሪኩን ሰፋ አድርጎ ያቀርባል
   ለ. ልቦለድ በሚያነሳው ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮር ይገባዋል።
   ሐ. የገፀባህሪያትን አካላዊና ህሊናዊ ሁኔታ ባልተቆጠበ መንገድ ያቀርባል።
   መ. ታሪኩ ሰፋ ያለ ጊዜና ቦታን ይጠይቃል።

4. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች መካከል ስለ አጭር ልቦለድ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የአጭር ልቦለድ ገፀባህሪይ በታሪኩ ውስጥ በርካታ ግጭቶች ይገጥሙታል።
   ለ. አጭር ልቦለድ ደራሲው የራሱን ፍልስፍና ዘርዘር አድርጎ እንዲያቀርብ ያስችለዋል።
   ሐ. አጭር ልቦለድ የረጅም ልቦለድ አንድ ምዕራፍ ሊሆን ይችላል።
   መ. የአጭር ልቦለድ ጭብጥ ነጠላ /አንድ/ ነው።

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ጭውውት

"በእውኑ ዓለም በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ የሐሳብ ወይም የንግግር መለዋወጥ አለ። ሁለት ሰዎች ባላቸው ግንኙነት መሠረት በየአጋጣሚው የሆነ ጉዳይ ላይ ሲነጋገሩና ሐሳብ ለሐሳብ ሲለዋወጡ አንሰማለን። እንዲህ ያለው የሐሳብ መለዋወጥ በልብወለድ ገፀ ባህርያትም ይደረጋል። ይህም የሐሳብ መለዋወጥ ምልልስ /ጭውውት/ በመባል የሚታወቀው ነው።"

*ምንጭ (ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሑፍ መሠረታውያን፣ (2000)።*



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDR[E] Not to be rep[roduced]

፩. መምህራችሁ በሚጠቁሟችሁ አንድ ረጅም ልብወለድ ውስጥ በምልልስ (ጭውውት) መልክ የቀረበውን አንድ ክፍል በአንድ ገጽ ላይ ቀንጭባችሁ በጽሑፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፪. በምልልስ የቀረበ የአንድ ልቦለድ ታሪክ መርጣችሁ አንብቡና በቡድን ሆናችሁ በመለማመድ ክፍል ውስጥ በጭውውት መልክ አቅርቡ፡፡

፫. በምዕራፍ አንድ ላይ በተማራችሁት መሠረት የሚከተሉትን ሀቅ አዘል ዓረፍተ ነገሮች ወደ ግል አስተያየት ለውጣችሁ ተናገሩ፡፡

1. ብዙዎቹ ጋዜጠኞች ሙያዊ ስልጠና ወስደዋል፡፡
2. ጋዜጣ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን የመገናኛ ብዙኃን ዘርፎች ናቸው፡፡
3. በሬዲዮ ከሚቀርበው ዜና ይልቅ በቴሌቪዥን የሚቀርበው የተሻለ መረጃ ይሰጣል፡፡
4. ህዝባዊ ድጋፍ የሌላቸው መገናኛ ብዙኃን ዓላማቸውን ማሳካት ይሳናቸዋል፡፡
5. ማንኛውም ሰው መረጃ የመስጠትና የመቀበል መብት አለው፡፡

## ክፍል ሦስት፡- መጻፍ

### ከመጻሕፍት መረጃ ማግኘትና ማስታወሻ መውሰድ

ከልዩ ልዩ የመረጃ ምንጮች ሃሣቦችን ማግኘት ይቻላል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ከመጽሐፍ የምናገኘው መረጃ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ቤተ መጽሐፍት ውስጥ በመሄድ የካርድ ካታሎግ አፈላለግ ሥርዓትን ከኃላፊው/ዋ ጠይቆ በመጠቀም የምንፈልገውን መረጃ ማግኘት እንችላለን፡፡ በዚህም ወቅት በማስታወሻችን በአጭር በአጭሩ ፍሬ ሃሣቡን፡-

ሀ. በሐረግ ደረጃ፣

ለ. በዓረፍተ ነገር ደረጃ መያዝ ይኖርብናል፡፡

ይህ ተግባር ከጋዜጣ፣ ከመጽሔቶች፣ ከንግግር አድራጊዎች፣ ወዘተ ማስታወሻ በምንወስድበት ጊዜም ይጠቅመናል፡፡ ይህን የወሠድነውን ማስታወሻ ደጋግመን በማንበብና በስርዓት በማጠናቀር ለፈለግነው ጉዳይ በመረጃነት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡

*(በደበበ ኃ/ጊዮርጊስ እንግዳ ፣ ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ፣ (1999)፡፡*

**፩. ቀጥሎ የቀረበው አንቀጽ ሲያስተላልፈው የፈለገውን መልዕክት ከሁለት ዓረፍተ ነገሮች ባልበለጠ አሳጥራችሁ ጻፉና ተወያዩበት፡፡**

በባህሮችና በተራራዎች ላይ ባሉት ከተሞችና ሜዳዎች የሚታየው ነገር ሁሉ ያስጎመጃል፡፡ ሲያዩት ከቶ አይሰለችም፡፡ ተክሎችና አበባዎች፣ ዛፎች፣ ፍሬዎች፣ ስዕሎችና ቅርጾች፣ በብዙ ዓይነት ቋንቋ የተጻፉ ጋዜጣዎችና ልዩ ልዩ የሆኑ መጻሕፍት፣ ፋብሪካዎችና ማዕድኖች፣ መንገዶች፣ በየሱቁ የሚታዩት እቃዎችና የውበት መደብሮች ሁሉ ሲያዩዋቸው የሰው እጅ ያልዳሰሳቸው ይመስላሉ፡፡

## የአንቀጽ ቅርጾች


በጥሩ ሁኔታ የተጻፉ አንቀጾች ሁሉ ኃይለቃል አላቸው፡፡ ኃይለቃል የአንቀጽን ማእከላዊ ሃሳብ የያዘና አብዛኛውን ጊዜ በአንቀጹ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ዓረፍተነገር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን እንደ ጸሐፊዎች ምርጫ ኃይለቃሉ በአንቀጹ መሃል ወይም መጨረሻ ላይም ሊመጣ ይችላል፡፡ ኃይለቃል፣ ርዕሳዊ ዓረፍተነገር፣ መሪ ዓረፍተነገር፣ መንደርደሪያ ዓረፍተነገር የሚሉ ስያሜዎች አሉት፡፡

አልፎ አልፎ የአንቀጹን ርዝማኔ ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ኃይለቃሉን በአንቀጽ ውስጥ ሁለት ጊዜ ማቅረብ የማቻልበትም መንገድ አለ፡፡ ሆኖም ሁለቱ ኃይለቃሎች በተለያየ መልክ /አባባል/ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡


የአንቀጽ ቅርጾችም በኃይለቃሉ መገኛ ቦታ ይወሰናሉ፡፡ ቀጥሎ የቀረቡትን ስዕላዊ መግለጫዎች ለአብነት እንመልከት፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced


ሀ. ኃይለ-ቃል በስተመነሻ





ለ. ኃይለ-ቃል በስተመድረሻ




ሐ. ኃይለ-ቃል በስተመነሻና በስተመድረሻ




መ. ኃይለ-ቃል በመሃል




፪. **ቀጥለው የቀረቡላችሁን ምንባቦች በጥሞና ካነበባችሁ በኋላ በተማራችሁት መሠረት የአንቀፅ ቅርፃችን አመልክቱ።**

### ምንባብ 1

እስክንድር ራሱን አከከ። ሰው ሰራሽ ጥርሱንም ወደ ውስጥ ገፋ አደረገ። ከሲራክ ባሻገር መስኮቱን ዘልቆ ሩቅ ተመለከተ። ዐይኑ፣ ከአድማስ ጋር

ተጋጨ፡፡ የነበረው ተሰጥዖ ከጉም ጋር በንኖ ሲጠፋ ታየው፡፡ አንድ ወር፣ ግፋ ቢል ሁለት ወር… ስሙን የያዘው መጽሐፍ ታትሞ… ሰው እጅ ገብቶ ሲነበብ ለማየት የነበረው ተስፋ፣ ይታየው የነበረው ጣፋጭ ሕልም… በሲራክ ክፋት ምክንያት… ድንገት መጥፎ ቅዠት ሆኖ ሲቀር… ደብዛው ሲጠፋ…ሲጨልም… የጋራ ስሜቱ ከስሎ አመድ ሲሆን ታየው፡፡ ሕይወት መራራ ሆነችበት፣ ሲራክን ከልቡ ጠላው፡፡ ልቡን በጦር ቢወጋውም ምንኛ ደስ ባለው ነበር፡፡

## ምንባብ 2

"ነፍጠኞች ለምዳቸውን እየደረቡ በጢስ የበለዘ ጋሻና ጦር ይዘዋል፡፡ ጎልማሶች የክትክታ ቆመጥና የወይራ ዱላ ይዘዋል፡፡ መቆነን የሚያበዙት እነዚያ የጐንደር ደብተሮች እንደመልካም ክፍክፍ ጥምጥማቸውን ቀሽረው ጭራቸውን እያወዛወዙ እርስ በርሳቸው በማንጎራጎር በጓድ በጓድ ይከማቻሉ፡፡ ወዲያውኑ ከፋሲል ግንብ አንስቶ እስከ ጉፋያ መስጫ ድረስ ሕዝብ ጥቅጥቅ ብሎ መላ ጥቁር ቆብ፣ ቢጫ ቆብ፣ ክምር ጥምጥም፣ የሚያንፀባርቅ በራ፣ በቅቤ ወዝ የሚጭረቀረቅ ቁንዳላ፣ ከቆብ አስጥሉ ላይ ሆኖ ለተመለከተ የሚታየው የሰው ጭንቅላት ብቻ ነበር፡፡ አንዳንዱ የባሰበት በመዳፉ ጮራዋን ሲጋርድ ሁሉም አንጋጦ የፋሲልን ግንብ ሰገነት ይጠባበቃል፡፡ ጎንደር ተሞሽራ ሙሽራዋን ትጠብቃለች፡፡ ከሕዝቡ ብዛት ጋር ሲመዛዘን ብዙ ድምጽ አልነበረም፡፡ ነጋሪቱ ብቻ "ገብር፣ገብር" እያለ ያስተጋባል፡፡ ድንገት ቀጥ አለ አካባቢውን ፀጥታ ዋጠው፡፡ ሰው ከተረከዙ ወደጣቱ፣ ከአንድ እግሩ ወደሌላው በመንቆራጠጥ በያለበት ይቁነጠነጥ ጀመር፡፡ ወደላይ አንጋጦ የሚጠባበቀው ሕዝብ ስሜት በገሀድ የሚታይ ቢሆን ኖሮ ክንፍ አውጥቶ የሚበር በመሰለ ነበር፡፡ ከዚያም ያደገደገ ጥቁር ጎፈሬ በጥቂት ሰዎች ታጅቦ ወጣና የተጠቀለለውን ብራና ገልጦ አነበበ፡፡

## ምንባብ 3

ሶፍያና ጽጌ መንታዎች ናቸው፡፡ እናታቸው ብርሃነ በተወለደች በአሥራ ሦስት ዓመቷ አግብታ በአሥራ ስድስት ዓመቷ እነሱን ወለደች፡፡ መንትዮቹ ከተወለዱ በኋላ አራት ቀን ብቻ ቆይታ ሞተች፡፡ አባታቸውም

ተድላ የሚስቱ ሬሳ ሲወጣ አብሮ እንደወጣ የደረሰበት አልታወቀም፡፡ ስለዚህ ሶፍያን ደብረሊባኖስ ገዳም መንኩሰው የሚኖሩ እማሆይ ጥሩነሽ የሚባሉ የእናቷ ታላቅ እህት ወስደው ያሳድጓት ጀመር፡፡ ተዋበችም በኃይሉ ደበበ የሚባል የአባቷ ታላቅ ወንድም በእድሜው ከእሷ ምንም ያህል ከማይበልጥ ዮናታን ከሚባል ልጁ ጋር አብሮ ያሳድጋት ጀመር፡፡

## ምንባብ 4

ዮፍታሔ ለሁለተኛ ጊዜ ኤልያስን ላይመለስበት ጥሎ የወጣው በእናቱ ምክንያት በተፈጠረው ሐሜት ነበር፡፡ ቄሰ ገበዝ ንጉሴና ወይዘሮ ማዘንጊያ የተጋቡት ሥርዓተ-ተክሊል ደርሶላቸው ሥጋ-ወደሙ ተቀብለው ነበር፡፡ ሞት ቢለያቸውም ሕጋቸው እንደፀና ይኖራል እንጂ መፍረስ አልነበረበትም ሕጋዊ ባላቸው በሞት ሲለዩዋቸው መንኩሰው፣ እማሆይ ተብለው ባይመነኩሱም ሕጋቸውን አክብረው፣ አጽንተው ጊዜ ሞታቸውን መጠበቅ ነበረባቸው፡፡ እሳቸው ግን ይህን አላደረጉም፡፡ ከባላቸው አንፃር ገና ወጣት የሚባሉ፣ የደም ገንቦ የሆኑ ወይዘሮ፣ በዚህም ላይ ደግሞ ሙቀት ልምላሜ ያልጠፋባቸው ቀበጥ ሴት ስለነበሩ ህጋዊ ባላቸው እንደሞቱ በመመንኮስ ወይም አድበው፣ ጨምተው በመቀመጥ ፈንታ እንደሚባለውም ብዙ ሳይቆዩ ሕጋቸውን አፈረሱ፡፡ የቄሰ ገበዝ ንጉሴ ቤተሰብ ተበጠበጠ፣ ተከፋፈለ፡፡ የኤልያስም ሕዝብ፣ በተለይ የደብተራው ወገን ደህና አድርጎ ዘፈነበት፡፡ ይህም አሳዛኝ ሁኔታ ሥሱ በሆነው በዮፍታሔ ስሜት ውስጥ የኀዘንና የብስጭት ማዕበል ፈጥሮ ሕሊናውን እንደመታው መንፈሱን እንዳቃጠለው፣ ነፍሱን እንዳዋከባት ማስተዋል አያዳግትም፡፡ ደብተራውና የቅኔ ባልንጀሮቹ የዘፈኑበት በተራ ግጥም አይደለም፡፡ በለዘበ፣ በረቀቀ፣ ሲያቃጥል፣ ጠቅ ሲያደርግ፣ በሚያንገበግብ፣ ቅስም በሚሰብር፣ ውቃቢ በሚገፍ ቅኔ ሳይሆን አልቀረም፡፡ በቅኔ መሰደብ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ በተለይም በጥበቡ፣ በኪኑ ታሽቶ ላደገው ብሩህ ለሆነው ለዮፍታሔ የማይዋጥ ነገር ሆነ፡፡ በእናት ምክንያት የተጀመረው ሐሜት በልጅ ስደት ተፈጸመ፡፡

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ክፍል አራት:- ሰዋስው

### አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት/ሐረጋት

አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ቃላትን ከቃላት፣ ሐረጋትን ከሐረጋት፣ ዓረፍተ ነገሮችን ከዓረፍተ ነገሮች ወዘተ. የሚያያይዙ ወይም የሚያሸጋግሩ ቃላት ማለት እንደሆኑ ብዙ ጸሐፍት ጽፈዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ባየ ይማም በ2002 ካሳተሙት "አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው" ውሰጥ የሚከተለው ይገኛል፡፡

- አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት (ሐረጋት) የሚጠቁሙት ነገርን፣ ድርጊትን፣ ባህሪን ወዘተ አይደለም፡፡ በመሆኑም በራሳቸው ትርጉም የላቸውም ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ተግባር አላቸው፡፡ ተግባራቸው ከስም በፊት ወይም በኂላ መገኘትና ስሙን ከሌላ ነገር ጋር ማዋደድ ወይም ማያያዝ ነው፡፡ እንዳገባባቸው ዓይነት፣ ከስም በፊት ወይም በኂላ የሚገቡ ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ከስም በፊት የሚገቡት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| አያያዥ ቃል | ምሣሌ |
|---|---|
| ስለ | ስለ ገንዘብ |
| እንደ | እንደ ሰው |
| ወደ | ወደ ጎጃም |
| እስከ | እስከ መርካቶ |

- ከስም በፊትና በኋላ የሚገቡት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው፡፡

| አያያዥ ሃረግ | ምሣሌ |
|---|---|
| ከ ___ አጠገብ | ከ ተማሪ አጠገብ |
| ከ ___ ማዶ | ከ ወንዝ ማዶ |
| ከ ___ ወዲህ | ከ አጥሩ ወዲህ |
| እስከ___ ድረስ | እስከ ጐጃም ድረስ |

© MoE, FDRE Not to be reproduced

**፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አንብባችሁ በትዕዛዙ መሠረት ሥሩ፡፡**

1. መምህራችሁ በሚያዟችሁ አንድ ረጅም ልብወለድ ከሚገኝ አንድ ምዕራፍ በተከታታይ ሁለት ገጾች ውስጥ የሚገኙትን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
2. ያገኛችኋቸውን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ከላይ ባያችኋቸው ምድቦች ውስጥ በመከፋፈል ዘርዝራችሁ አሳዩ፡፡

### የዓረፍተ ነገር ዓይነቶች

ዓረፍተ ነገር ማለት በሥርዐት ተቀነባብሮ ሙሉ ስሜትን ሊሰጥ የሚችል የቃላት ወይም የሐረጋት ስብስብ ነው፡፡ ዓረፍተ ነገሮች ተራ ወይም ውስብስብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. **ተራ ዓረፍተ ነገር፡-** ከአንድ ስማዊ ሀረግና ከአንድ ግሣዊ ሐረግ ብቻ ይዋቀራል፡፡

   **ምሳሌ፡-** ታፈሰ ሣር አጨደ፡፡
   ስሐ ግሐ

2. **ውስብስብ ዓረፍተ ነገር፡-** ይህ ዓረፍተ ነገር ከአንድ በላይ ማሰሪያ አንቀጽ የያዘ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ዋናው መለያው በውስጡ የያዘው የግስ መጠን ነው፡፡ ይህን ለመረዳት የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

   ሀ. ልጁ ምሳውን በላ፡፡
   ለ. ልጁ ወደ ት/ቤት ሄደ::

እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች በተለያየ መልክ በማጣመር ወደ ውስብስብ ዐረፍተ ነገር መለወጥ ይቻላል፡፡

ስ.ሐ ግ.ሐ

**ምሳሌ ፡-** 1. ልጁ ምሣውን በልቶ ወደ ት/ቤት ሄደ፡፡
2. ልጁ ምሣውን እንደበላ ወደ ት/ቤት ሔደ፡፡

**፪. ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች "ተራ" ወይም "ውስብስብ" በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. ያ ልጅ ጎበዝ ተማሪ ነው፡፡ ______________________

ለ. አስቴር አባቷ ስለመጡ ተቀበለቻቸው፡፡______________________



© MoE, FDRE Not to be reproduced

ሐ. ከበደ ከመቀመጫው ፈጥኖና በርግጎ ተነሳ፡፡____________

መ. ወንድሙ ወደውጭ ሀገር ስለሄደ ቶሎሳ አዘነ፡፡________

ሠ. ህጻን ልጅ ወተት በጣም ይወዳል፡፡ ____________

## የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች

ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንጻር ስንመረምራቸው ሁለት ጠባዮች ይታይባቸዋል፡፡ ከእነዚህም አንዱ የመዝገበ ቃላት ወይም ቀጥተኛ ፍች የመያዛቸው ጠባይ ሲሆን ይህም እማሬያዊ ፍች ይባላል፡፡ ሁለተኛው ቃላት ከቀጥተኛ ፍቻቸው በተጨማሪ በተደራቢነት የሚይዙት ምስጢራዊ ወይም ስውር ፍች ሲሆን ይህም ፍካሬያዊ ፍች ይባላል፡፡

**ምሳሌ**

| ተ.ቁ | ቃል | እማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1 | መሬት | ምድር፣ ዓለም | ቻይ |
| 2 | ዶማ | መሬት መቆፈሪያ የእጅ መሳሪያ | የማይገባው |
| 3 | መሰላል | መወጣጫ | ረጅም/ቀውላላ |
| 4 | መብረቅ | ብልጭታ ነጎድጓድ | ኃይለኛ አስደንጋጭ |

፩. ከላይ የቀረበውን ማብራሪያና ምሳሌ መሠረት በማድረግ በሰንጠረዡ ውስጥ ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቻቸውን ሙሉ፡፡

| ተ.ቁ | ቃል | ዕማሬያዊ ፍች | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| 1 | እርግብ | | |
| 2 | አመድ | | |
| 3 | እባብ | | |
| 4 | እሾህ | | |
| 5 | እሳት | | |
| 6 | ቆቅ | | |
| 7 | ምላጭ | | |

© MoE, FDRE Not to be reproduced

## ክፍል አምስት:- ሥነጽሑፍ

### የልቦለድ አላባውያን

የልቦለድ አላባውያን የሚባሉት ታሪክ፣ ትልም፣ ገጸባህሪይ፣ ግጭት፣ መቼት ጭብጥ እንዲሁም አንጻር የተሰኙት ናቸው። በዚህ ምዕራፍ መቼት እና ጭብጥን እንመለከታለን።

**መቼት**:- ‹‹መቼት›› የሁለት ቃል ጥምረት ነው። ቃላቱም ‹‹ መቼ?›› እና ‹‹የት?›› የሚባሉት ናቸው። በዚህ መሠረት፣ የልቦለድ መቼት ሲባል ታሪኩ የተፈጸመበት ዘመንና ቦታ ማለት ነው።

**ምሳሌ:-** ሰፈራችን እንደሸረሪት ድር ተወሳስበው የቂርቆስን ቤተክርስቲያን ከከበቡት ቤቶች የበስተ ምስራቁን አቅጣጫ ይዛ ተመስርታለች። … ዓሳ ይመስል ከተንሿጠጠች ቤቴ ወጣሁ:: ቀኑ ጨፍግጎታል። የቂርቆስ ቤተክርስቲያን ጥንጁት እንደሚታጠን ጋን ጉም ያንዣብብበታል። ዞር ብዬ ቤቴን አየኋት። …

*/አለማየሁ ገላጋይ፣ ቅበላ 2001፣3::/*

ከላይ ባየነው ምሳሌ የታሪኩ አካባቢ ተጠቅሶ እናገኛለን። ይኸውም የገጸ ባህሪው የመኖሪያ አካባቢ ቂርቆስ ቤተክርስቲያን አካባቢ እንደሆነ በትረካው ተነግሮናል። የጊዜው ጨፍጋጋነትም ተጠቁሟል።

**ጭብጥ:-** ደራሲው በህብረተሠቡ ውስጥ ያየውን፣ የታዘበውን፣ የተገነዘበውን ማህበራዊ ጉዳይ በማንሳት አመለካከቱን እውቀቱን መሠረት አድርጎ በልቦለዱ አንድ መልዕክት ያስተላልፋል። ይህ ደራሲው እንዲተላለፍ የፈለገው ፍሬ ነገር ጭብጥ ይባላል።

ጭብጥን ለይቶ ለማውጣትና ለመገንዘብ ከባድ ነው። በአንድ ቦታ ወይም አንቀጽ ላይ ቁልጭ ብሎ አናገኘውም። አንባቢ ታሪኩን አንብቦ ሲጨርስ በታሪኩ ከቀረቡ የተለያዩ የገጸ ባህሪያት ንግግሮችና አስተያየቶች መነሻነት ጭብጡን ፈልቅቆ ሊያወጣና ሊገነዘብ ይችላል።



© MoE, FDRE Not to be reproduced

፩. መምህራችሁ የሚጠቁሟችሁን አንድ ረጅም ልቦለድ አንብባችሁ የልቦለዱን መቼት እና ጭብጥ በመለየት ክፍል ውስጥ አቅርቡ።

፪. ቀጥሎ የቀረቡትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች ግለጹ።

| | |
|---|---|
| ሀ. አሳሩን በላ። | ረ. እጀ-ሰባራ፣ |
| ለ. ፀጉር ስንጠቃ፣ | ሰ. ክንዱን ተንተራሰ። |
| ሐ. ፊቱን ነጨ። | ሸ. አራስ ነብር፣ |
| መ. ሰው ሆነ። | ቀ. ሱሪ ባንገት፣ |
| ሠ. እንባ ጠባቂ፣ | በ. ነፈሰበት። |

፫. ከተለያዩ ጽሑፎች ፈሊጣዊ አባባሎችን ከነፍቻቸው በመፈለግ ሰብስባችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## ፈሊጣዊ አነጋገር

ፈሊጣዊ አነጋገር ማለት አንድ ሐሳብ ከመደበኛው/ከቀጥታ/ አገላለጥ በተለየ መልኩ ክብደትና ውበትን ተጎናጽፎ ለአድማጭ እንዲደርስ የሚያደርግ የአነጋገር ስልት ነው። ፈሊጦች የተናጋሪውን ቋንቋ ውበትና ለዛ በማላበስ የአድማጭን ስሜት የሚኮረኩሩ ቅመሞች ናቸው።

**ምሣሌ፡-** ተናደደ ለማለት ደሙ-ፈላ፣ ፊቱ ቀላ፣ አበደ፣ የሚሉትን ፈሊጦች እንጠቀማለን።

ፈሊጥ አንድ ቃል ብቻውን ወይም ቃልና ቃል የሚመሰርቱት ሊሆን ይችላል።

**ምሳሌ፡-** ፊት ነሣኝ /አገለለኝ፣ አራቀኝ/
ለዋሳ /ልፍስፍስ/
ሰማይ ቅርቡ /ወሬኛ፣ የተግባር ሰው ያልሆነ/
ቀኝ እጅ /መከታ፣ አለኝታ/

© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDR
Not to be rep

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር የረጅም ልብወለድ ምንነትና ከአጭር ልብወለድ ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት በንጽጽር ለማየት ችለናል፡፡ በልብወለድ ውስጥ መቼትንና ጭብጥን ለይተን የማውጣት ልምምድ ሰርተናል፡፡ የተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ምንነት፣ ከተሰጠ ጽሑፍ ውስጥ ደግሞ ተራና ውስብስብ በማለት ዓረፍተ ነገሮችን ለይተን አስቀምጠናል፡፡ የቃላት እማሬያዊ ፍች ማለት ጥሬ ፣ የዘወትር ወይም ግልጽ ትርጉም ማለት እንደሆነ ፤ ፍካሬያዊ ፍች ማለት ደግሞ ቃላት ካላቸው እማሬያዊ ትርጉም በተጨማሪ ይዘውት የሚመጡ ተጨማሪ ትርጉም እንደሆነ ለማየት ችለናል፡፡ መሸጋገሪያ ቃላትንም ሆነ አያያዥ ቃላትንና ሐረጋትን ከጽሑፍ ውስጥ ለይተን ማውጣት ተለማምደናል፡፡ የአንቀጽ ቅርጽንም ትርጉም ተረድተን የተሰጡ አንቀጾችንም አንብበን በስዕላዊ መግለጫ ማስቀመጥም ችለናል፡፡ በመጨረሻም ፈሊጣዊ ንግግሮች እንዴት እንደሚመሰረቱና ፍቻቸው ምን እንደሆነ እየተረጐምን መለማመዳችን ይታወሳል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ያነበባችኋቸውን ልቦለዶች ረጅምና አጭር ልብወለድ በሚሉ አምዶች ሥር ዘርዝራችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡
2. ካነበባችሁት ረጅም ልብ ወለድ ወይም በሬድዮ ከተከታተላችሁት የረጅም ልብወለድ ትረካ ውስጥ የአንዱን ጭብጥና መቼት ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡
3. ተራ ዓረፍተነገር ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ በመስጠት አስረዱ፡፡
4. ውስብስብ ዓረፍተነገር ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌ ስጡ፡፡
5. የሦስት ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በንጽጽር ዓረፍተነገር በመሥራት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡
6. በሚከተሉት አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት /ሐረጋት/ ዓረፍተነገር መስርቱ፡፡
   ሀ. እንጂ  ለ. ከዚያም በኋላ  ሐ. ቢሆንም
7. የሚከተሉትን ፈሊጣዊ ንግግሮች ትርጓሜ በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸው፡፡
   ሀ. የትየለሌ  ለ. አጉራ ዘለል  ሐ. ኩታ ገጠም
   መ. አውራ ሌሊት  ሠ. ሥጋ ለስጋ

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለልቦለድ ምንነት የሚያስረዳውን ምንባብ ሀሳብ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 2. | የረጅም ልቦለድንና የአጭር ልቦለድ ምንነትና ልዩነት ተገንዝቤአለሁ፡፡ | | | |
| 3. | የመቼትንና የጭብን ምንነት ለይቻለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ተራና ውስብስብ ዓረፍተነገሮችን መለየትና መጻፍ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 5. | ለቃላት አማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 6. | አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላትን ለይቻለሁ፡፡ | | | |
| 7. | እውነታና የግል አስተያየት የሆኑትን ለይቻለሁ፡፡ | | | |
| 8. | የተለያዩ የአንቀጽ ቅርፃች መኖራቸውን አውቄአለሁ፡፡ | | | |
| 9. | በኃይለ ቃልና በዝርዝር ዓረፍተነገሮች መካከል ልዩነት እንዳለ ተረድቻለሁ፡፡ | | | |
| 10. | ለፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍች እሰጣለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

© MoE, FDR
Not to be rep